

# ነፃ የጉንፋን ክትባትዎን ዛሬ ያስይዙ

## ይከተቡ

የኢንፍሉዌንዛ (ፍሉ) ስርጭት ከፍተኛ ደረጃ የሚደርስበት ጊዜ የበጋ ወቅት ነው፣ ስለዚህ የፍሉ ወቅት ከመግባቱ በፊት የነጻ የፍሉ ክትባትዎን መውሰድዎ ጥሩ ሀሳብ ነው። በአካባቢዎ ባለ GP፣ በማኅበረሰብ ጤና ክሊኒክ ወይም መድሀኒት መደብር መከተብ ይችላሉ።
እድሜያቸው ከ6 ወራት በላይ ለሆነ ለማናቸውም ሠው የፍሉ ክትባት እንዲወስድ ይመከራል። የሜዲኬር ካርድ

ከሌለዎት በኲዊንስላንድ ውስጥ እስከኖሩ ድረስ የነጻ የፍሉ ክትባት መውሰድ ይችላሉ።

## ክትባቱ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

ኢንፍሉዌንዛ ኣንዳንድ ሰዎችን በጣም እንዲታመሙ ሊያደር የሚችል በጣም ተላላፊ በሽታ ነው። ሆስፒታል መተኛት እና ሞትን ጨምሮ ከባድ ችግሮች ሊያስከትል ይችላል።

ለሆስፒታል መተኛት በጣም የተጋለጡ ሰዎች ትናንሽ ልጆች፣ አዛውንቶች፣ እርጉዝ ሰዎች እና እንደ የስኳር በሽታ፣ የሳንባ ወይም የልብ ችግር ያሉ የጤና እክል ያለባቸው ሰዎች ናቸው።

ሁሉም ሰው ክትባት ማግኘቱን በማረጋገጥ ኢንፍሉዌንዛን መከላከል በጣም አስፈላጊ ነው፣ በተለይም ለአደጋ የተጋለጡትን።

ህጻናትን ማስከተብ በሽታው ወደ ሌሎች ሠዎች የሚኖረውን ስርጭት ለማስቆም ያግዛል።

## ክትባት ለአዲስ የኲንስላንድ ነዋሪዎች

አዲስ ወደ አውስትራሊያ ለሚመጡ የፌደራል መንግስት የክትባት ፓስፖርቶችን እና የድሮ የክትባት ሰነዶችን ለመተርጎም ነፃ አገልግሎት ይሰጣል። ለበለጠ መረጃ፣ ወደ Department of Home Affairs Translating Service (የቤት ውስጥ ጉዳይ ተርጓሚ አገልግሎት ክፍል) ይሂዱ ወይም በ 1800 962 100 ይደውሉ።

## የፍሉ ክትባት ሃላል ወይ ኮሸር ነው ወይ?

ክትባቶች ለሃይማኖተኛ ሙስሊም ልጆች (ሃላል) እና ሃይማኖተኛ የአይሁድ ልጆች (ኮሸር) ይፈቀዳሉ። ተጨማሪ መረጃ በ Institute for Vaccine Safety (የክትባት ደህንነት ተቋም) ድህረ ገጽ ላይ ይገኛል።

## ተጨማሪ መረጃ ይፈልጋሉ?

የፍሉ ክትባት ስለሚያገኙበት ሁኔታ ማናቸውም ጥያቄዎች ካሉዎት፣ ከራስዎ GP ጋር ይነጋገሩ።

በተጨማሪም ለ**13 HEALTH** በስልክ ቁጥር **13 43 25 84** ደውለው ከነረስ ጋር መነጋገር ይችላሉ።

አስተርጓሚ ካስፈለገዎት እንዲመደብልዎት ይጠይቁ። ስለ ኢንፍሉዌንዛ ክትባት ተጨማሪ መረጃዎችን እና እርስዎ በሚናገሩት ቋንቋ የተዘጋጁ መረጃዎችን

እዚህ ሊያገኙ ይችላሉ።

Search for

Vaccination Matters

Queensland Government